አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.12
Addis Ababa. 10th August, 2017

## ማውጫ

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ**
**ደንብ……………………ገጽ ሺ፩፻፷፯**

## CONTENTS

**The Addis Ababa City Government Regulation to Direct and Regulate the Non-formal Trade Activity**
**Regulation ……………………….Page 1167**

## ደንብ ቁጥር፹፰/፪ሺ፱
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ

በከተማችን በመካሄድ ላይ ያለው መደበኛ ያልሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በመምጣቱ በዘርፉ በርካታ ሰዎች በተለይም ወጣቶችና ሴቶች ሲሳተፉበት በመታየቱ፤

በዚህ አይነት የንግድ ሥራ ውስጥ የተሠማሩ ዜጎች ለራሳቸው የሥራ ዕድል ፈጥረው በመገኘታቸው እና የንግዱ አካሄድ የህጋዊ ነጋዴዎችን ገበያ በማይሻማ መልኩ ሥርአት በማስያዝ በቀጣይ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት የሚሸጋገሩበት መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## REGULATION NO. 88/2017
## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENTREGULATION TO DIRECT AND REGULATE THE NON-FORMAL TRADE ACTIVITY

**Whereas**, the non-formal trade activity carried out in the city has been expanding over time and many people, especially, the youth and women, have been involving in the sector;

**Whereas**, citizens who are involving in such trade activity have been found that they had created their own job opportunity and to normalize such a trade system shall not harm the market of traders who are working under the law and it has been found necessary to facilitate ways to transform the thereof to the formal trade system in the future;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ዘርፉ በግብይት ሥርአቱ ውስጥ ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶት በሥርዓት መምራት በማስፈለጉ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫ንዑስ አንቀፅ (፩) (ረ)እና በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፹፬መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ ቁጥር ፹፰/፪ሺ፱ዓ.ም››ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩ ‹‹**አስተዳደር**››ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪ ‹‹**የንግድ ሕግ**›› ማለት በ፲፱፻፶፪ ዓመተ ምህረት የወጣው የንግድ ሕግ ነው፤

፫ ‹‹**አዋጅ**›› ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፰ ነው፤

፬ ‹‹**ቢሮ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ ነው፤

፭ ‹‹**የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት**››ማለት በአስተዳደሩ አደረጃጀት መሠረት በሁለተኛ የእርከን ደረጃ የሚገኝ የንግድ ጽህፈት ቤት ነው፤

**Now**, **therefore**, as it has been found necessary to recognize the sector in the trade system and to direct it systematically, in accordance with article 23 sub-article (1) (f) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/1995 (as amended) and article 84 of the Addis Ababa City Government Exective and Municipal Service Organs Establishment Proclamation No. 35/2004 (as amended) has issued this regulation as follows.

## Part One
## General Provisions

### 1. Short Title

This regulation may be cited as the‹‹ Addis Ababa City GovernmentRegulation to direct and regulate the non-formal trade activity regulation No. 88/2017.››

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. **‹‹Government››** means the Addis Ababa City Government;
2. **‹‹Commercial Code››** means the commercial code which was ratified in the 1960;
3. **‹‹Proclamation››** means the commercial registration and business licensing proclamation number 980/2016;
4. **‹‹Bureau››** means the trade bureau of the Addis Ababa city government;
5. **‹‹Office of the Sub-city››** means the trade office in the second stratum in accordance with the structure of the city;

፮. **‹‹የወረዳ ጽሕፈት ቤት››**ማለት በአስተዳደሩ አደረጃጀት መሠረት በሶስተኛ የእርከን ደረጃ የሚገኝ የንግድ ጽህፈት ቤት ነው፤

፯. ‹‹**መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ**›› ማለት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበና የንግድ ፈቃድ የሌለው መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ወይም ለመሠማራት የሚፈልግ እስከ ብር ፲ሺ. /አሥር ሺ. ብር/ ካፒታል ያለው ይህን ደንብና አግባብነት ያላቸውን ህጎች አክብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው፤

፰. ‹‹**መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ**›› ማለት በመደበኛው የንግድ ህግ ወይም አዋጅ የማይመራ ቀላል የንግድ ሥራ ሲሆን ግለሰቡ በአዋጁ መሠረት ሳይመዘገብና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም ቋሚ የንግድ ቤት ወይም ቦታ ሣይኖረው በዚህ ደንብ መሠረት በጎዳና፣ በአደባባይ በከፊል በየመንገዱ ዳርቻ በሚገኝ ትንንሽ ተለጣፊ እና ተንጠልጣይ የዕቃ መደርደርያ ይዞ እስከ ብር ፲ሺ. /አሥር ሺ.ህ ብር/የሚገመት በአነስተኛ ካፒታል የሚሠራ የንግድ ሥራ አይነት ነው፡፡ ሆኖም በግብርና፣ በእደ-ጥበብ የተሠማሩ ሰዎች ምርታቸውን ቢሸጡ ይህ ትርጉም አይመለከታቸውም፤

፱. ‹‹**መዝገብ**›› ማለት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚመዘገቡበት በቢሮው የሚዘጋጅ ዋና ወይም ባህረ መዝገብ ነው፤

6. **‹‹Office of the Woreda››** means the trade office in the third stratum in accordance with the structure of the city;

7. **‹‹Non-Formal Trader››** means an individual who is not registered according to the commercial registration and business licensing proclamation and does not have a business license and involves in the non-formal trade activity or who wants to engage in the sector having a capital of birr 10,000.00 (ten thousand birr) and willing to work by obeying this regulation and the relevant laws;

8. **‹‹Non-Formal Trade Activity››** means a simple trade activity which is not governed by the existing commercial code or proclamation; which is carried out by a small capital up to birr 10,000.00 (ten thousand birr) on the streets, roundabouts, partly in small kiosks on the road side without proper registration based on the proclamation and not having a business license or not having a permanent business place. However, this definition shall not describe those individuals who are involving in agriculture and handicraft who are selling their product;

9. **‹‹Record››** means a main record prepared by the bureau so as to register those individuals who are involving in the non-formal trade activity;

፲. ‹‹**ቋሚ የንግድ ቦታ**›› ማለት ተለይቶ ለንግድ የተመደበ ወይም የተዘጋጀ ለንግድ ሥራ ቀን፣ ሰዓት እና የሥራ ዘርፍ (መስክ) ፕሮግራም የወጣለትና በዚሁ መሠረት ሳይቋረጥ ቦታው ለልማት እስኪፈለግ ድረስ መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

፲፩. ‹‹**ጊዚያዊ የመነገጃ ቦታ**›› ማለት ለንግድ ሥራ ቀንና ሰዓት ፕሮግራም ያልተያዘለት የንግድ ዘርፍ ወጥቶለት ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጁ ጎዳናዎች አደባባዮች በጊዜያዊነት መደበኛ ያልሆነ ንግድ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

፲፪.‹‹**መደበኛ ያልሆነ ጽዳት**›› ማለት የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በመደበኛነት በዕቅድ ከሚያፀዳቸው የተለያዩ ቦታዎች፣ ጎዳናዎች፣ መንገዶች፣ ደሴቶች በተለየ ሁኔታ መደበኛ ያልሆነ ንግድ የሚካሄድባቸውን ሥፍራዎች በሙሉ ሥራውን ተከትሎ ግብይቱ በተወሠነለት ዕለትና ሠዓት ከተከናወነ በኋላ በልዩ ሁኔታ የሚካሄድ የጽዳት ሥራ ነው፤

፲፫.‹‹**በማዕከል የሚካሄድ ድጋፍ እና ቁጥጥር**›› ማለት መደበኛ ያልሆኑ የንግድ ሥራ እንዲካሄድ በተፈቀደበት ቦታ፣ ጎዳና፣ መንገድ፣ ደሴት ውስጥ የሚደረግ ድጋፍ እና ቁጥጥር ነው፤

፲፬.‹‹**ከማዕከል ውጪ የሚካሄድ ድጋፍና ቁጥጥር**››ማለት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ እንዲካሄድ ከተፈቀደበት ቦታ፣ ጎዳና፣ መንገድ፣ ደሴት ውጪ ባልተፈቀደ ቦታ የሚካሄድ ድጋፍ እና ቁጥጥር ነው፤

10. **‹‹Permanent Market Place››** means a place allocated or prepared for the trade and in which a program is scheduled for thedate, time and business type of the non -formal trade activity and such continues as per the thereof until the site is needed for development;

11. **‹‹Temporary Market Place››** means a place where the non -formal trade activity is being carried out, having set the business type, on the roads and roundabouts which are prepared for such activity where the day and time fir the trade activity is not programmed;

12. **‹‹Non-Formal Sanitation››** means a sanitation activity especially carried out in all the places where non-formal trade activity is held followed by its happening as per the specified day and time of the thereof by the sanitation administration agency, in a special condition, out of its regular and planned cleaning of the various places, avenues, roads and roundabouts;

13. **‹‹Supervision and Regulation Conducted Centrally››** means a supervision and regulation conducted at places, avenues, roads and traffic circles where a non-formal trade activity is allowed to be carried out;

14. **‹‹Supervision and Regulation Conducted beyond Centrally››** means a supervision and regulation conducted out of the places, avenues, roads and traffic circles where a non-formal trade activity is not allowed to be carried out;

፲፭.‹‹የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ›› ማለት በደረት ላይ የሚንጠለጠል ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ በተተረጎመው መሠረት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለሚሠራ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ በበጀት አመቱ የተሰጠ ወይም የታደሰ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሠረት ያለቅጣት የሚታደስበት ጊዜ ያላላፈበት የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ወይም መለያ ነው፤

፲፮.‹‹አስተዳደራዊ እርምጃ››ማለት ይህን ደንብና አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች ተላልፎ በሚገኝ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ ላይ እንደአስፈላጊነቱ በቢሮው ወይም በክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤትአማካይነት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ እስከ መሠረዝ የሚወሰድ እርምጃ ነው፡፡

፫. <u>አላማ</u>

የዚህ ደንብ ዓላማ፡-

፩. መደበኛላልሆነየንግድሥራ እውቅና በመስጠት የሥራው ዘርፍ የሚመራበትን ስርዓት በማዘጋጀት ለኢኮኖሚውና ለማኀበራዊ እንቅስቃሴ አጋዥ እንዲሆን ማስቻል፤

፪. በዘርፉየሚታዩት ችግሮች ለማስወገድና ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ ወደ መደበኛ ንግድ ስርዓት እንዲገባ ማስቻል ነው፡፡

15. **‹‹Transitional Period Permit or ID››** means a transitional period permit or ID which is given to a non-formal trader who carries out a non-formal trade activity in the current fiscal year or a renewed one according to the definition set in sub-article 8 of this article or the one that its renewal period with penalty does not expire according to article 16 of this regulation;

16. **‹‹Administrative Measure››** means a measure taken by, as may be necessary, the bureau or office of the sub-city or woreda on the non-formal trader who disobeys this regulation and other relevant directives from giving a verbal warning to revocation of the transitional period permit or ID.

3. <u>Objective</u>

The objective of this regulation is:

1. To enable the non-formal trade activity supportive of the economy and social activities through giving recognition and preparing a system for managing the sector.
2. To alleviate the exhibited problems of the sector and enable the thereof to be involved in the formal trade system by providing support.

**፬.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራላይ በተሠማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ምዝገባ</u>

**፭. <u>መዝገብ ስለማቋቋም</u>**

፩.በቢሮው የሚተዳደር ከተማ አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የሚመዘገብበት መዝገብ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪.ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኝ መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማናቸውንም ሰው ይመዘግባል፡፡

**፮. <u>ስለመመዝገብ</u>**

፩.ማንኛውም ሰው በመዝገብ ሳይመዘገብ በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ በየትኛውም ቦታ መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

፪.ማንኛውምሰውበመዝገብየሚመዘገበው በሚሠራበት አካባቢ በሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

፫.ማንኛውምሰው በመዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

**4. <u>Scope of application</u>**

This regulation shall be applicable on any individual who is involving in the non-formal trade activity within the region of the Addis Ababa city government.

## <u>Part Two</u>

## <u>Registration</u>

**5. <u>Record Establishment</u>**

1. A record, which is used to register any individual who is involving in the non-formal trade activity, that is governed by the bureau and applicable to city wide, shall be established by this regulation.
2. The bureau shall register any individual who is engaged in the non-formal trade activity within the city government according to this regulation.

**6. <u>About to be Registered</u>**

1. Any individual shall not be allowed to involve in a non-formal trade activity in any place within the region of the city government without being registered on the record.
2. Any individual shall be registered on the record in the office of the woreda near where he works.
3. Any individual shall be registered only once on the record.

**፯.የምዝገባ መስፈርት**

መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ አመልካች የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ቅጽ ጋር በማያያዝ በሚሠራበት አካባቢ በሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፩. አመልካቹ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው ፪ (ሁለት) ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤

፪. አመልካቹ በአስተዳደሩ ውስጥ ከሚኖርበት ወረዳ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወረቀት፤

፫. ከግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የተሰጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤ እና

፬. አመልካቹ በአሁኑ ወቅት በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ ወይም ሌላ ማንኛውም ሥራ ላይ ያልተሠማራ ሥራ አጥ መሆኑን በአስተዳደሩ ውስጥ ከሚኖርበት ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የጽሁፍ ማስረጃ፡፡

፭. አመልካቹ ይህን ደንብ እና ደንቡን ተከትሎ የሚወጣውን መመሪያ አክብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆኑን በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**፰. ስለምዝገባ ማመልከቻና ውሳኔ አሰጣጥ**

፩. ማንኛውም መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቢሮው ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በማያያዝ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፪. ማናቸውምለምዝገባየቀረበማመልከቻተቀባይነትያለ ውሆኖከተገኘ የወረዳው ጽሕፈት ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱(፩) መሠረት የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

**7. Registration Requirement**

An applicant who wants to involve in a non-formal trade activity shall present the following documents attached with the application form to the office of the woreda where he works:

1. Two (4*4) photographs of the applicant which are taken within six months period;
2. A renewed ID card from the woreda where the applicant lives;
3. Tax Payer Identification Number (TIN) given by the office of the tax collector;
4. A written testimony from the office of the woreda administration where the applicant lives that justifies he is not currently involved in a formal trade activity or he is not involved in any other work and is unemployed;
5. The applicant shall ensure, in his application that he is willing to obey working under this regulation and directives to be issued following this regulation.

**8. Registration Application and Giving Decision**

1. Any individual who wants to involve in a non-formal trade activity should fill the application form prepared by the bureau together with attaching the evidences stated under article 7 of this regulation and submit it to the woreda office before starting the business.
2. If the submitted application for registration is accepted, the woreda office shall register and give a transitional period permit or ID that will be put on the merchant's chest after receiving the specified payment according to article 19 (1) of this regulation.

፫. ቢሮው ለምዝገባ አገልግሎት የሚውሉ ወጥ ቅፆችን ያዘጋጃል፤በክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት አማካይነት ለወረዳ ጽሕፈት ቤት እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡

፬. ማንኛውምበመደበኛየንግድሥራላይየተሰማራ ሰው ወይም በአዋጁ መሠረት በንግድ መዝገብ የተመዘገበ ነጋዴ በዚህ መዝገብ መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

፱ የምዝገባ መረጃዎችን ስለማስተላለፍ

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዘገባ መረጃዎችን በየዕለቱ ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ያስተላልፋል፣ የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት በሁለተኛው ቀን ለቢሮው ያስተላልፋል፡፡

፪. ቢሮውበዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ፩ መሠረት የተላለፈለትን የምዝገባ መረጃዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት መዝግቦ ይይዛል፡፡ እንደአስፈላጊነቱበሚዘጋጅሶፍትዌርዘመናዊየመረጃአያያዝላይይመዘግባል፡፡

፲.እውቅና ስለመስጠት

በዚህ ደንብ መሠረት ተመዝግቦ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሕጋዊ ሆኖ አንስተኛ የንግድ ሥራ የሚሠራ መሆኑ በዚህ ደንብ መሰረት እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

3. The bureau shall prepare similar forms used for the registration purpose; make sure that it reaches to the woreda office via the office of the sub-city.
4. It is prohibited to register any individual on this record who is involved in a formal trade activity or a trader registered on a business record according to the proclamation.

**9. Transferring Registration Information**

1. The woreda office that carried out the registration based on this regulation shall transfer the registration information daily to the sub-city using a form prepared for such a case. The office of the sub-city shall also transfer the thereof to the bureau on the second day.
2. According to sub-article 2 of article 5 of this regulation, the bureau shall register and keep registration information that are transferred to it according to sub-article 1 of this article.

**10. Giving Recognition**

Any individual who is registered as per this regulation and was given a transitional period permit or ID which is put on the chest shall be recognized legally to carry out a small business activity in accordance with this regulation.

## ፲፩.ስለምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ

፩.ማንኛውም ሰው የንግድ ሥራውን ለማካሄድ ከተመዘገበበት እና ከተመደበበት የሥራ ቦታ አካባቢ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አካባቢ ለመለወጥ ከፈለገ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና ፰ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት በቅድሚያ ያደረገውን ምዝገባ ማሰረዝና ከወረዳው ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት መመለስ፣ በቀጣይ መሸኛ ወረቀት በመውሰድ ወደ መረጠው አካባቢ የሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት በመሄድ መሸኛውን በማቅረብ ሌላ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በመውሰድ መነገድ ይችላል፡፡

፪.ማንኛውምሰው ተመዝግቦ የሚሰራውን የንግድ መስክ አይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ከፈለገ የተመዘገበበት ወረዳ ጽሕፈት ቤት በመቅረብ በቢሮው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የሚሠራውን የንግድ መስክ አይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ይችላል፡፡ 1175

፫.የምዝገባለውጥወይምማሻሻያ ስለመቅረቡ እና ተቀባይነት ስለማግኘቱ፡ የወረዳው ጽሕፈት ቤት ማረጋገጫ መስጠትና እና ተቀባይነት ያገኘበትን ቀን፣ ስለምዝገባው ለውጥ ወይም ማሻሻያ በዝርዝር በመግለጽ ለአመልካቹ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህ የጽሑፍ ማረጋገጫ ካልተሰጠ በስተቀር የቀረበው የምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ እንደተለወጠ ወይም እንደተሻሻለ አይቆጠርም፡፡

## 11. Registration Change or Improvement

1. Any individual should get his prior registration cancelled and return his transitional period permit or ID put on the chest to the woreda office that had issued the thereof if he wants to change his registered and assigned work place to another in accordance with sub-article 2 of article 6 and sub-article 2 of article 8 of this regulation. Then he can start his business by submitting the testimonial paper that he had received to the woreda office of his preference and getting another transitional period permit or ID.

2. Any person shall appear at the office of the woreda that he has registered and fill a form prepared by the bureau if he wants to change or improve the already registered business type being carried out to another one.

3. The office of the woreda shall give assurance for the submittal of the registration change or improvement and acceptance of the thereof; and notify the date of acceptance and registration change or improvement to the applicant and relevant stakeholders in writing in detail. The submitted registration change or improvement shall not be considered as replaced or upgraded unless the written assurance is given.

## ፲፪. ምትክ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ስለመስጠት

፩. መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ምዝገባ ያደረገ ማንኛውም ሰው የተሰጠው የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ከሆነ ቀደም ሲልለሰጠው የወረዳ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ በማመልከት ምትክ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ማግኘት ይችላል፡፡

፪. የሽግግርጊዜፈቃድ ወይም መታወቂያ የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የተበላሸውን ይመልሳል፡፡

፫. ወረዳው ማመልከቻ ሲቀርብለት ለጠፋው ወይም ለተበላሸው የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በዚህ ደንብ በደንብ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጣል፡፡

## ፲፫. ከመዝገብ ስለመሰረዝ እና አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ከመዝገብ ይሰረዛል፤

፩.የንግድ ሥራውን ከተወ፤

፪.ከሞተ፤

፫.ሐሰተኛመረጃወይምሰነድአቅርቦመመዝገቡ ከተረጋገጠ፤

፬.ከተፈቀደለትናበመታወቂያውላይከተገለጸው ቦታ ወይም ቀን ወይም ሰዓት ወይም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ውጪ ወይም ባልተፈቀደ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ከተገኘ፤

## 12. Issuance of A Replacement Transitional Period Permit or ID put on the Chest

1. Any individual who has registered for the non-formal trade activity that has lost or possesses a worn-out transitional period permit or ID may get a replacement by applying to the office of the woreda that had issued the thereof in writing.

2. Any individual should return the worn-out transitional period permit or ID when he requests for a replacement.

3. The office of the woreda shall collect the specified payment in the regulation and give the replacement ID for the lost or worn-out transitional period permit or ID when an application for the thereof is submitted.

## 13. Revocation from a Record and Taking Administrative Measure

Any individual who is involved in a non-formal trade activity shall be revoked from the record due to the following reasons:

1. Termination of the trade activity;
2. Death;
3. Being found registered using fraud information or document;
4. If found working in contrary to the permitted and described place, date, time or the non-formal trade activity on the ID or involving in a trade activity that is not allowed;

፭.ቢሮው ወይም የወረዳጽሕፈት ቤቱየሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክል እና በወቅቱ ያላቀረበ እንደሆነ፤

፮.የሸማቹንየጤናናየጽዳትአጠባባቅ፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ የንግድ ዕቃውን ጥራት ወይም አይነት ደረጃ ካጓደለ ወይም ሌላ ሕገ ወጥ ተግባር ከፈጸመ ወይም በኮንትሮባንድ የገቡ ዕቃዎች ወይም የራሱ ያልሆነውን በአዋጁ መሠረት በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ነጋዴ ዕቃ ይዞ ከተገኘ፤

፯.ደረትላይየሚንጠለጠልየሽግግርጊዜፈቃድወይም መታወቂያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ካልታደሰ፤

፰.ሸማቹን በማታለል ወይም በማሳሳት ተግባር ላይ ከተገኘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ይህን ደንብ የጣሰ እንደሆነ፣

ቢሮውአጥፊውንከመዝገብይሰርዛል፡፡ አጥፊውም ቢሮውየሰጠውንደረትላይየሚንጠለጠልየሽግግርጊዜፈቃድወይምመታወቂያተመላሽያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ አሠጣጥ

### ፲፬.የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ አሠጣጥ

፩. በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራን ሰው የመመዝገብና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የመስጠት ሥልጣን የቢሮው ነው፤

5. If fails to correctly and timely submit information required by the bureau or the woreda office;
6. If fails to meet the quality or type or standards of health and hygiene safety, environmental protection of the consumer and the commodity or service; or committing other illegal activity or possessing contraband goods or other goods owned by a trader involving in a formal trade activity according to the proclamation;
7. If the transitional period permit or ID put on the chest is not renewed according to sub-article 2of article 16 of this regulation;
8. If found in any act of cheating or misleading the consumer or violates this regulation in any other condition, the bureau shall revoke the guilty party from the record; denies the transitional period permit or ID put on the chest that was given to him.

## Part Three
## Issuance of the Transitional Period Permit or ID

### 14. Issuance ofthe Transitional Period Permit or ID

1. According to this regulation, the bureau shall have the power to register and issue a transitional period permit or ID put on the chest to an individual involving in a non-formal trade activity.

፪. ቢሮ በሚሰጠው ውክልና መሠረት የወረዳ ጽሕፈት ቤት በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራን ሰው ይመዘግባል፣ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ያደርጋል፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የሰጠውን የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ያግዳል፣ ይሠርዛል፡፡

2. The office of the woreda, as per the authority given by the bureau and according to this regulation, shall register an individual involving in a non-formal trade; give and renew the transitional period permit or ID put on the chest; control and supervise the thereof; take administrative measures; suspend or revoke the issued transitional period permit or ID if found necessary.

**፲፭.በተመዝጋቢ የሚሠራ መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ዝርዝር**

መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የሚሠራው መደበኛ ያልሆነ የንግድ የሥራ አይነት፣ የሥራ መስክ ወይም የሥራ ዘርፍ ዝርዝር በሕግ የተፈቀደ መሆን ይገበዋል፡፡ በተጨማሪም ይህ አይነቱ የንግድ ሥራ የሙያ ብቃት መረጋገጫና መስፈርት የማያስፈልገው የንግድ ሥራ አይነት መሆን አለበት፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ከሆነ ግን ማረጋገጫውን ማቅረብ አለበት፡፡

**15. List ofthe Non-Formal Trade Activities Carried Out by the Registered Client**

The lists of the business types or activities carried out by the individual who is involving in a non-formal trade activity should be permitted by law. In addition, such type of business should not require a professional competency assurance and a criterion. If it demands so, the assurance should be presented.

**፲፮. ደረት ላይ ስለሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የተሰጠ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ካልተሠረዘ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት እስከታደሰ ድረስ የፀና ይሆናል፡፡

**16. Effective Date and Renewal of the Transitional Period Permit or ID put on the Chest**

1. The transitional period permit or ID which is issued as per sub-article 2 of article 8of this regulation shall be effective if it is renewed according to sub-article 2 of this article and unless it is revoked due to the listed reasons under article 13 of this regulation.

፪. መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራ ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ደረት ላይ ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የበጀት አመት ካበቃ በኋላ ባለው ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ፴ ቀን ድረስ ከግብር አስከፋይ መስሪያ ቤት ክሊራንስ በማቅረብ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ተገቢው ክፍያ ተከፍሎ በየአመቱ በመዝጋቢው አካል መታደስ አለበት፡፡

፫. በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ (፩) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ደረት ላይ ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያውን ሳያድስ የቀረ ሰው በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ውስጥ ማለትም ከጥር ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ድረስ ባሉት ወራት የመደበኛ የሽግግር ፈቃድ ወይም መታወቂያ ማሳደሻ ክፍያ እጥፍ ብር ፻ /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ፈቃዱን ማደስ ይችላል፡፡

፬. በዚህአንቀጽ መሠረት የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያውን ያላሳደሰ ሰው ከመዝገብ ይሰረዛል፡፡ ተመዝጋቢው የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይምመታወቂያ መመለስ አለበት፡፡ ካይመልስ ቢቀር በእጁ እንዳለ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡



2. The registerer shall renew the transitional period permit or ID, which was issued to the individual who is involving in the non-formal trade, annually within six months (from July 8 to January 7) following the end of the fiscal year having a clearance from the tax collection authority and collecting the relevant payment according to sub-article 2 of article 19 of this regulation.

3. If an individual fails to renew his transitional period permit or ID put on the chest within the indicated period under sub-article 1 of this article, he may renew the thereof in the next six months (from January 9 to July 7) having paid birr 100.00 (one hundred birr) which is double of the regular transitional period permit or Id renewal fee.

4. According to this article, an individual who does not renew the transitional; period permit or ID shall be revoked from the record. The individual should return the thereof back. If he fails to do so, it shall no longer be in service.

**፲፯.የተመዘገበና ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ**

ማንኛውም በዚህ ደንብ መሰረት የተመዘገበና ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው፡-

**፩.መብቶች**

ሀ. በመዝገብ ያስመዘገበውን እና የተፈቀደለትን መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ማካሄድ፤ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ መውሰድ፤

ለ. የተሰጠው የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ምትክ መውሰድ፤

ሐ. የሚነግደውን መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የሚነግድበት ቦታ ወይም አካባቢ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት አሳውቆ የመለወጥ፣ የማሻሻል፤

**፪. ግዴታዎች እና ክልከላዎች**

ሀ. በዚህ ደንብ መሠረት በውክልና መመዝገብም ሆነ ምዝገባውን ማደስ የተከለከለ ነው፤

ለ. ወረዳው በተፈቀደለትና በመደበው ቦታ፣ ዕለት፣ሰዓት፣እና የሥራ ዘርፍ ላይ ብቻ መሥራት አለበት፤

ሐ. መደበኛ ላልሆነንግድ ሥራ የሚይዛቸው ዕቃዎችንጥራት፣ መጠን፣ ይዘት መለወጥ ወይም ማጓደል፣ ሸማቹን እና ተጠቃሚውን ማጉላላት የለበትም፤

መ.መደበኛ ላልሆነ ንግድሥራየሚይዛቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች፣የገዛበትን ህጋዊ ደረሠኝ ማቅረብ አለበት፤

ሠ. ለሸማቹና ለተጠቃሚው ተገቢውን ክብር መስጠት አለበት፤

**17. <u>Rights and Obligations of the Individual who was Registered and Possess the Swinging Transitional Period Permit or ID</u>**

According to this regulation, any individual who was registered and possesses the swinging transitional period permit or ID:

1. **Rights**
   a. Carry out the registered and permitted non-formal trade activity; have his transitional period permit or ID;
   b. Having a replacement if the issued transitional period permit is lost or damaged;
   c. Changing or improving the type of non-formal trade activity and place or area through notifying the office of the woreda.

2. **Obligations and Restrictions**
   a. According to this regulation, it is prohibited to register or renew the thereof through delegation;
   b. Carry out the trade based on the permitted or assigned place, day, time and business type by the woreda;
   c. Not altering or reducing the quality, amount or content of the goods that he possesses for the non-formal business; not harassing the consumers and users;
   d. Keep legal receipt for purchasing industrial products for his non-formal trade activity;
   e. Showing proper respect for consumers and users;

ረ. የተሳሳቱ ወይም ተመሳስለው የተሰሩ ምርቶችን መሸጥ የለበትም፤

ሰ. የብቃት ማረጋገጫ ወይም መስፈርት የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች መያዝ የለበትም፤

ሸ. ከመዝጋቢው አካል የተሰጠውን ተንጠልጣይ መለያ ወይም መታወቂያ በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ አንገቱ ላይ በማጥለቅ በግልጽ እንዲታይ ማድረግ፤

ቀ. የተሰጠውን ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ እንዳይበላሽ በጥንቃቄ መያዝ፤ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም፤

በ. በመዝጋቢው አካል መረጃ ሲጠየቅ መረጃውን ወዲያው መስጠት አለበት፤

ተ. መደበኛ ያልሆነንግድ ሥራውን ሲጨርስ አካባቢውን በአግባቡ ማጽዳት አለበት፤

ቸ. የአካባቢውን ንጽህና፣ ፀጥታና ደህንነት መጠበቅ አለበት፤

ኀ. ባልተፈቀደ ቦታ መነገድና የትራፊክ እንቅስቃሴ ማወክ የለበትም፤

ነ. በዚህ ደንብ መሠረት የተመዘገበ ሰው በአዋጁ መሠረት መመዝገብና የንግድ ፈቃድ ማውጣት የለበትም፡፡

**፲፰.ድጋፍና ቁጥጥር ስለማድረግ**

፩. የወረዳው ቁጥጥር ባለሙያዎች የተመዘገበና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው ግዴታዎቹን በትክክል መወጣቱንና በዚህ ደንብ መሠረት ሥራው መካሄዱን ለማረጋገጥ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

፪. ቢሮውወይም ጽሕፈት ቤት ለቁጥጥር ሥራ የሚያሠማራው የቁጥጥር ሠራተኛ የተሰጠውን የመስሪያ ቤት መታወቂያ መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራው ሠው በቅድሚ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

f. Not selling false or fake products;

g. Not possessing products that demand competency assurance or criterion;

h. Putting the swinging label or ID which was given by the registerer around the neck and make it clearly visible while on duty;

i. Keeping the issued swinging transitional period permit or ID from damage; not passing the thereof for another party to use it;

j. Provide information promptly up on the request of the registerer;

k. Properly clean the place when finishing the non-formal trade activity;

l. Keep the hygiene, peace and security of the surroundings;

m. Have the obligation not to sell at unpermitted places and not to disturb the traffic flow;

n. An individual who is registered according to this regulation, should not be registered and possess a trade license as per the proclamation.

**18. Providing Support and Inspection**

1. Inspectors of the woreda shall inspect and provide support so as to ensure whether the registered individual who was given the swinging transitional period permit or ID put on the chest is fulfilling his obligation properly and the business is being carried out as per this regulation or not;
2. Any inspection officer of the bureau or office that carries out the inspection should show his work place ID first to the individual who is involving in a non-formal trade activity.

## ክፍል አራት
## የክፍያመጠንናየባለድርሻአካላትሚና

**፲፱.የክፍያ መጠን**

፩.ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ መዝገብ ላይ ለመመዝገብ እና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የሚወስድ ሰው ለምዝገባና ለመታወቂያ አገልግሎት ብር ፸ /ሰባ ብር/ ይከፍላል፡፡

፪.ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ መዝገብ ላይ የተመዘገበና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ወይም መታወቂያ የወሰደ ሰው ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታቂያውን ለማሳደስ ብር ፶ /ሃምሳ ብር/ ይከፍላል፡፡

**፳.ከቢሮው ጋር በመተባበር ይህን ደንብ የሚያስፈጽመው አስፈፃሚ አካላት ዝርዝር፣ ተግባር እና ኃላፊነት**

፩. ከዚህ በታች የተጠቀሱት የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት በቢሮው አስተባባሪነት በጋራ እና በቅንጅት ይሠራሉ፣

ሀ. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፤

ለ. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፤

ሐ. የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን፤

መ.የደንብ ማስከር አገልግሎት ጽህፈት ቤት፤

ሠ.የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፤

ረ.የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፤

## Part Four
## Payment Amount and Stakeholders Contribution

**19. Payment Amount**

1. Any individual who wants to register in a non-formal trade record and get the transitional period permit or ID shall pay birr 70.00 (seventy birr) for registration and ID service.

2. Any individual who wants to register in a non-formal trade record and get the transitional period permit or ID shall pay birr 50.00 (fifty birr) for the renewal of the thereof.

**20. List, Duties and Responsibilities of the Executive Bodies that Implement this Regulation in Cooperation with the Trade Bureau**

**1.** The following stated executive bodies of the city government shall work together and in collaboration with the bureau under the cooperation of the thereof:

A. Land Development and Management Bureau;
B. Traffic Management Agency;
C. The Addis Ababa Roads' Authority;
D. Office of The Code Enforcement Service;
E. The Addis Ababa City Police Commission;
F. Sanitation Administration Agency;

ሰ. የኮሙኒዩኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፤

ሸ. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፤

ቀ. የምግብ፣ የመድሀኒትናየጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤

በ. የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ባለሥልጣን፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከቱት የከተማው አስፈፃሚ አካላት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ.፬ (እንደተሻሻለ) የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ እንደ የድርሻቸው የሚከተሉትንተግባራት ይፈፅማሉ፡፡

**፫.የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፡-**

የመነገጃ ቦታ ዝግጅት በተመለከተ የከተማው ፕላን በሚፈቅደው የመሬት አጠቃቀምና አግባብ ያላቸው ሕጎችን መሠረት በማድረግ በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ወዳልሆነንግድ ለሚገቡ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ የመነገጃ ቦታዎች በማጥናት ይለያል፣ የመነገጃ ቦታ ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ከቢሮው ጋር በመሆን መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይለሚሠማሩ ሰዎች የሥራ ቦታ ይፈቅዳል፡፡



G. Communication Affairs Bureau;

H. Micro and Small Scale Enterprises Development Bureau;

I. Food, Pharmaceuticals and Health Protection, Administration and Inspection Authority;

J. The Addis Ababa City Revenue Authority.

**2.** Without prejudice to the power and duties given to the Addis Ababa city government executive and municipal service organs re-establishment proclamation number 35/2012 (as amended), the executive organs of the city, indicated in this regulation under sub-article 1 of this article, shall implement the following duties respectively.

**3. Land Development and Management Bureau**

Concerning the preparation of a business place, study and identify a permanent and temporary business place for individuals who are going to be involved in thenon-formal trade activityas per this regulation based on the land utilization and ratified laws set by the city’s plan; prepare and assign business places; permit business places for those who are going to engage in the business together with the trade bureau.

**፬. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፡-**

ከከተማው የትራንስፖርትእና የትራፊክ እንቅስቃሴ ጋር አጣጥሞ መደበኛ ያልሆኑ ንግድ ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን አካባቢዎች የመለየት ሥራ ይሠራል፤ አጠቃቀሙን ከቢሮው ጋር በጋራ ይሠራል፡፡

**፭. የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን፡-**

በከተማው ውስጥ የሚገኙ መንገዶችን ደረጃ በማውጣት በአካባቢው የሚገኙ የመንግስት፣ የሕዝብ፣ የአለም አቀፍ ተቋማት እና ልዩ የሥራ ባህሪ ያላቸው ሥፍራዎችን በመለየት መደበኛ ላልሆነ ንግድ ሥራ የተከለከለ፣ በከፊል የተፈቀደ እና የተፈቀደ በማለት ይለያል፡፡ የለያቸውን ጎዳናዎች፣ መንገዶች፣ ደሴቶች ለቢሮው፣ ለፖሊስ ኮሚሽን፣ ለደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፣ ለጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

**፮. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፡-**

ሀ. ከማዕከል ውጪ የሚካሄድ የንግድ ቁጥጥር ያካሂዳል፤

ለ. በዚህ ደንብ መሠረት የፀና የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ያልያዘ ሰው በማንኛውም ባልተፈቀደ ቦታ የንግድ ሥራ እንዳያከናውን ይከላከላል፡፡

**4. Traffic Management Agency**

Identify places for carrying out the non-formal trade activity in line with the transport and traffic flow of the city; work together with the bureau for the implementation of the thereof;

**5. Addis Ababa Roads Authority**

Set standards for the roads of the city and identify the places in the vicinity as governmental, public, worldwide institutions and special purposed; and label the thereof as prohibited for non-formal trade activity, partially permitted and permitted. Notify the identified boulevards, roads and roundabouts in writing for the bureau, police commission, office of the code enforcement service and sanitation administration agency.

**6. Office of The Code Enforcement Service**

A. Control the trade activities except the central one.

B. Prohibit any individual, who does not possess the transitional period permit or ID which is effective as per this regulation, not to carry out a trade activity in any unpermitted places.

**፯. የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን፡-**

በሌላሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለውን ተግባር ያከናውናል፡-

ሀ. በዚህ ደንብ መሠረት የሚነግድ ሰው በደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

ለ. ከተፈቀደለት አካባቢ ወይም ንግድ ሥራ ወይም ከተፈቀደለት ቀንና ሰዓት ውጪ የንግድ ሥራ ያለመስራቱንና የትራፊክ እንቅስቃሴ ያለማወኩን ይቆጣጠራል፤

ሐ.መደበኛ ያልሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበትን አካባቢ ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን ይቆጣጠራል፡፡

**፰. የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፡-**

ኤጀንሲው ልዩ የጽዳት ፕሮግራም በማውጣት በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ የሚካሄድባቸውን መንገዶችና አካባቢዎች መደበኛ የጽዳት ሥራ ጊዜውን ሳይጠብቅ ጽዳት ያካሂዳል፡፡

**፱. የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፡-**

ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት ስለመደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ሕጋዊነትና አሠራር ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎች ይሠራል፡፡

**7. Addis Ababa City Police Commission**

Without prejudice to the power and duties bestowed, it shall carry out the following activities:

A. Check that the individual that carries out this business, according to this regulation, possesses the swingingtransitional peried permit or ID put on the chest;

B. Control that the individual is not carrying out his business out of the permitted place, business type, day and time; and disturbing the traffic movement;

C. Make sure that the peace and security of the place for carrying out thenon-formaltrade activity is protected.

**8. Sanitation Administration Agency**

The agency shall clean the roads and its surroundings in which thenon-formal trade activity is carried out, as per this regulation, by setting special cleaning program without following the regular cleaning program.

**9. Communication Affairs Bureau**

The bureau, according to this regulation, shall carry out awareness creation activities about the legality and procedure of non-formal trade activities to the community.

**፲.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፡-**

ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች፡-

ሀ. የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት እና የገንዘብ ቁጠባ ባህላቸውን አዳብረው ወደ መደበኛው የንግድ ሥራ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤

ለ. የፋይናንስና ብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

**፲፩.የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፡-**

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከናወኑ መደበኛ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎችን አስመልክቶ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከምግብ እና ከጤና እንክብካቤ ጋርበተያያዘአስፈላጊውንቁጥጥር ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

**፲፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለሥልጣን፡-**

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሰረት፡-

ሀ. መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠዎች መክፈል ያለባቸውን ግብር ይወስናል፤ ይሠበስባል፤ የግብር ግዴታቸውን ለተወጡት ክሊራንስ ይሰጣል፤

**10. Small and Micro Scale Enterprises Development Bureau**

For those segments of the society who are involving in the non-formal trade activity, the bureau according to this regulation shall:

A. Cause the transfer of the thereof to the formal trade activity through providing various trainings and strengthening their savings habit;

B. Facilitate conditions for the thereof in order to get financial and loan services.

**11. Food, Pharmaceutical and Health Protection Administration and Inspection Authority**

The authority, based on the relevant laws, shall carry out the necessary inspection related to food and health protection concerning the non-formal trade carried out as per this regulation. If found necessary, take legal measures.

**12. The Addis Ababa City Revenue Authority**

According to this regulation, the authority shall:

A. Decide the tax to be paid by those individuals who are involved in the non-formal trade activity; collect the thereof; provide clearance for those who paid their tax.

ለ. መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራ ላይየተሰማሩ ሰዎች የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን እንዳይነግዱ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ ህጋዊ እርምጃም ይወስዳል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፩.አስተዳደራዊ እርምጃ

፩. ይህን ደንብ ጥሶ የሚገኝ ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ሰው እንደጉዳዩ አግባብ በቢሮው የሚወሰድበት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

፪. በዚህደንብአንቀጽ፯ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ ላይ የተጠቀሰውን ተላልፎ በየትኛውም አካባቢ ወይም ሥፍራ መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይቀጣል፤ ይዞት የሚገኘው ንብረት ወይም ዕቃ ተሸጦ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

### ፳፪. በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ

በዚህ ደንብ መሠረት በክፍለ ከተማው ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤት አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ቅጣት የተወሰደበት ማንኛውም ሰው እርምጃው ወይም ቅጣቱ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በአስተዳደራዊ እርከን ደረጃ ተዋረዱን

B. Prevent those individuals who are involved in the non-formal trade not to sell contraband goods; control the thereof; take legal measures.

## Part Five

## Miscellaneous Provisions

### 21. Administrative Measure

1. Without prejudice to the administrative measure taken by the bureau, any person who was registered in the non-formal trade activity record and that violates or transgresses this regulation, shall be punished in accordance with the relevant penal code as per the case.

2. Any individual that violates the indicated points under sub-article 1 of article 6 and sub-article 2 and 3 of article 16 and found carrying out a trade activity in any place shall be punished by the relevant penal code; the property or goods in his possession shall be sold and the income shall be deposited to the government.

### 22. Submitting Grievance on the Administrative Measure

In accordance with this regulation, any person to whom an administrative measure or penalty has been taken may submit his grievance in writing hierarchically to the

በመጠበቅ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት፣ ለክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም ለቢሮው አቤቱታ በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት አካል በ፲(አስር) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበለት አቤቱታ መልስ በጽሑፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሣወቅ አለበት፡፡

**፳፫.ደንቡንስለማሻሻል**

ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**፳፬.ተጠያቂ ስለመሆን**

በዚህ ደንብ የተጣለበትን ኃላፊነትና ግዴታ ያልተወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፭.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፮.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮውይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፯.ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ህጐች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

woreda office, sub-city office or to the bureau within 15 working days starting from the day that the administrative measure was announced by the office of the sub-city or woreda. The body that accepted the grievance shall give its response to the complainant within ten (10) working days in writing.

**23. Amending the Regulation**

The cabinet may amend this regulation if it is found necessary.

**24. Liability**

Any person who does not fulfill his responsibility and obligation bestowed under this regulation shall be held liable according to the relevant laws.

**25. Duty to Cooperate**

Any person shall be duty bound to cooperate in executing this regulation.

**26. The Power to Issue Directives**

The bureau may issue a directive for the execution of this regulation.

**27. Inapplicable Laws**

Any regulation, directive or customary practice of the city government, which is inconsistent with this regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**፳፰.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፱ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስአበባነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓመተምህረት**

**ድሪባኩማ**

**የአዲስአበባከተማከንቲባ**

**28. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of August 10, 2017.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of August,2017.**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**